# የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

## በወጪ ፈንድ (መዋዕለ-ንዋይ) የሚደገፉ የምርምር እና አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች ትግበራ ለሚስተፉ ባለሙያዎች የማትጊያ ክፍያ ማሻሻያ መሪያ

## መመሪያ ቁጥር፡ 822/2013

ግንቦት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በውጭ ፈንድ ''የሚደገፍ የምርምርና አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች በማምጣት፣ በመምራት (በማስተባበር) እና በመተግበር ከመደበኛ ሥራ ጎን ለጎን ለሚሳተፉ ባለሙያዎች የማትጊያ ክፍያ ማሻሻያ የወስጥ መመሪያ''" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 1.ትርጓሜ

1.1. የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ኢ.ግ.ም.ኢ) ማለት የኢ.ግ.ም.ኢ ዋና ማስሪያ ቤትና በስሩ የሚገኙ ምርምር ማዕከላትን ያጠቃልላል፤

1.2. የውጭ ፈንድ (መዋዕለ-ንዋይ) ማለት ለምርምር እና አቅም ግንባታ መንግሥት ከሚመድበው በጀት ውጭ ለፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከለጋሽ ተቋማት የሚገኝ ገንዘብ ማለት ነው፤

1.3. ፕሮጀክት ማለት ከወጪ በሚገኝ መዋዕለ-ንዋይ ድጋፍ በተወሰነ ጊዜ ገደብ የሚተገበር የምርምር እና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ማለት ነው፤

1.4. የፕሮጀክት አስተባባሪ (Project Coordinator) ማለት በሚመለከታቸው የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎችና ዳይሬክተሮች የሚፈፀም አቅም እና የማኔጅመንት ልምድን መሠረት በማድረግ የሚመደብ በወጪ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶችን ትግበራ በበላይነት የሚመራ ወይንም የሚያስተባብር ተመራማሪ ነው፤

1.5. የፕሮጀክት ዋና (ግንባር ቀደም) ተመራማሪ (Project Principal Investigator) ማለት በውጭ ገንዘብ የሚደገፍ የምርምር እና አቅም ግንባታ ፕሮጀክትን ተፃፅፎ ያስገኘ ወይንም በተቋሙ የተገኘ ፕሮጀክትን በዋና ተመራማሪነት እንዲተገብር የምርምር ብቃትን መሠረት ባደረገ ግልፅ ማስፈርቶች በሚመለከታቸው የሙያ ዘርፉ ወይም የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች የተመደበ ተመራማሪ ማለት ነው፤

1.6. የፕሮጀክት ተባባሪ ተመራማሪ (Project Co-Principal Investigator) ማለት በሚመለከታቸው የተቋሙ የበላይ ኃላፊዎች ወይንም ፕሮጀክት አስተባባሪዎች ዋና (ግንባር ቀደም) ተመራማሪወን በፕሮጀክት ትግበራ

እንዲያግዝ የፕሮጀክቱን ዓላማ የሚፀምና የማስፈፀም አቅምን መሠረት ባደረገ ግልፅ ማስፈርቶች በረዳትነት የሚመደብ ተመራማሪ ነው፤

1.7. የፕሮጀክት ተጠሪ (Project Focal Person) ማለት የውጭ ፕሮጀክቶች የዕለት ተዕለት አፈፃፀም እንዲከታተል በሚመከተው የኢንስቲትየቱ የበላይ ኃላፊ ወይም ፕሮጀክት አስተባባሪ የፕሮጀክቱን ዓላማ የሚፀምና የማስፈፀም አቅምን መሠረት ባደረገ ግልፅ ማስፈርቶች የሚመደብ የኢንስቲትዩቱ ወይም የአጋር ተቋማት ተመራማሪ (ባለሙያ) ማለት ነው፤

1.8. የፕሮጀክት ማኔጅመንት ቡድን (Project Management Team) ማለት በውጭ ፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆኑ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ወይንም የአጋር ተቋማት ኃላፊዎችን፣ ተመራማሪዎችንና ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችን ያካትታል፡፡

## 2.የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት (ኢግምኢ) መሪነት ወይም ከሌሎች አጋር ተቋማት ጋር በትብብር በውጭ ፈንድ በሚተገበሩ የምርምርና አቅም ግንባታ ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

## 3.ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና አላማ ግልጽ፣ ፍትሀዊ እና ወጥ የማበረታቻ ሥርዓት በማዘርጋት የተመራማሪዎችን የስራ ሞራልና ተነሳሽነት በማጎልበት ተጨማሪ የምርምር ሀብት (መዋዕለንዋይ) እንዲገኝ ማበረታታትና ሲገኝም በውጤታማነት በመተግበር የተቋሙን የሚፈጸምና የማስፈጸም አቀም ማሳደገና ተልዕኮውን ለማሳካት እገዛ ማድረግ ነው፡፡

## 4.በመመሪያው የተካተቱ የማትጊያ አይነቶች

### 4.1.ወሎ አበል

በውጭ ፈንድ የሚደገፉ ፕሮጀክቶች የታለሙላቸውን ወጤት እንዲያስገኙ የፕሮጀክት ማኔጅመንት እና ተግባሪ የምርምር ቡድን አባላት የምርምር ሥራው በሚጠይቀው አግባብ ተንቀሳቅሰው

ሥራውን በዕቅዱ መሠረት ለመተግበር እንዲሁም የማስክ ጉዞዎችን ለማሳለጥ የሚያስችል ተመጣጣኝ፣ የመክፈል አቅምንና የሥራ ጫፍን ያገናዘበ የቀን የወሎ አበል የክፍያ ሥርዓት ማዘርጋት አስፈልጓል፡፡ የወሎ አበል ክፍያው በሦስት ፈርጅ እንደሚከተለው ተመድቧል፡፡

### 4.1.1 የተመራማሪዎች

በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ለምግብና መኝታ ወጪ የቀን ተመን ለተመራማሪዎች በተያዘው መደበኛ ወሎ አበል ላይ 50 በመቶ ተጨማሪ ተደርጎ ይከፈላል፡፡ በዚህ ስሌት ማስረት ለምሳሌ በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ተመን ለምግብ ወጪ ብር 200 (ሁለት መቶ) ይከፈል የነበረው በዚህ መመሪያ 50 በመቶ ተጨምሮ 300 (ሶስት መቶ) ብር ሲሆን ለመኝታ ወጪ ብር 200 (ሁለት መቶ) ይከፈል የነበረው ብር ደግሞ 300 (ሶስት መቶ) ብር ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሜልኩ በሁሉም የሥራ ደረጃ ለሚገኙ ተመራማሪዎች በመደበኛው የወሎ አበል ላይ 50% እየተጨመረ በሠንጠረዥ 1 በተመለከተው ማስረት ይከፈላል፡፡ በሁሉም የስራ ደረጃ ለሚገኙ ተመራማሪዎች ለመኝታ የሚከፈለው ገንዘብ በደረሰኝ ይወራረዳል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ የነባሩና የተሻሻለው የተመራማሪዎች የወሎ አበል ንጽጽር

| ተ.ቁ | የስራ መደቡ መጠሪያ | ነባር የወሎ አበል | የተሻሻለው የወሎ አበል |
|---|---|---|---|
| 1 | ጀማሪ ተመራማሪ | 400 | 600 |
| 2 | ረዳት ተመራማሪ I | 400 | 600 |
| 3 | ረዳት ተመራማሪ II | 400 | 600 |
| 4 | ተባባሪ ተመራማሪ | 600 | 900 |
| 5 | ተመራማሪ I | 600 | 900 |
| 6 | ተመራማሪ II | 600 | 900 |
| 7 | ከፍተኛ ተመራማሪ | 800 | 1200 |
| 8 | መሪ ተመራማሪ | 1000 | 1500 |

### 4.1.2 ለድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች

በውጭ ፕሮጀክቶች ትግበራ ሂደት ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸውና ለማስክ ሥራ ለማንቀሳቀሱ የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች (የማስክ ረዳቶች፣ የቴክኒክ ረዳቶች፣ ሾፌሮችና የአስተዳድር ባለሙያዎች) የቀን የውሎ አበል መጠን 500 (አምስት መቶ) ብር ይሆናል፡፡ አከፋፈሉም ለምግብ 250(ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር ሲሆን ለመኝታ ደግሞ 250 (ሁለት መቶ ሃምሳ) ብር ሆኖ ለመኝታ የሚከፈለው ገንዘብ በደረሰኝ ይወራረዳል፡፡

4.1.3 ለድጋፍ ሰጪ ዳይሬክተሮች

በውጭ የገንዘብ ድጋፍ በሚተገበር ፕሮጀክት በቀጥታ የሚሳተፍ በዳይሬክተርነት የተሰሙ የድጋፍ ሰጪ ኃላፊዎች በተራ ቁጥር 4.1.1 በተማከተው ስሌት መሠረት ሲቪል ሰርቪስ ለተመራማሪዎች በፈርጅ አንድ የተፈቀደው የቀን የውሎ አበል ላይ 50% ተጨምሮ 600 (ስድስት መቶ) ብር ይሆናል፡፡ አከፋፈሉም ለምግብ 300 (ሶስት መቶ) ብር እና ለመኝታ 300 (ሶስት መቶ) ብር ሲሆን ለመኝታ የሚከፈለው የውሎ አበል በደረሰኝ ይወራረዳል፡፡

## 4.2. የተለያዩ ሰነዶችን እና የጥናት ጽሁፎችን በአወደ ጥናት፣ ሴሚናር እና ሌሎች ሳይንሳዊ መድረኮች ለሚያቀርቡ ባለሙያዎች የማትጊያ ክፍያ

ተመራማሪዎችና የምርምሩን ሂደት ለማሳለጥ የጎላ ሚና ያላቸው ሰራተኞች ስልጠናዎችን በማዘጋጀትና ስልጠና በማስጠት፣ በተለያዩ የምርምር እና ልማት መድረኮች ሳይንሳዊ እና ምርምሩን ለማሳለጥ የሚረዱ መመሪያዎችን፣ ደንቦችንና ሰነዶችን በተቋሙ የበላይ ኃላፊዎችና ዳይሬክተሮች በሚሰጥ አቅጣጫ ለሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ከዚህ በታች በቀረበው መሰረት የማትጊያ ክፍያ ይፈፀማል፡፡

4.2.1. በአወደ ጥናት ላይ የጥናት ወጤቶችን ለሚያቀርቡ የወስጥም ሆነ የውጭ ባለሙያዎች በአንድ በቀረበ ጽሁፍ ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር)፤

4.2.2. ለፕሮጀክቱ ውጤማነት ሲባል ክህሎትን መሰረት በማድረግ ስልጠና እንዲሰጡ ተጋብዘው ስልጠናውን ለሰጡ የተቋማም ሆነ የአጋር ድርጅቶች ባለሙያዎች ከአንድ ቀን እስከ ሦስት ቀን ለሚሰጥ ስልጠና ብር 2,000 (ሁለት ሺህ)፤ ከአራት ቀን እስከ

ሰባት ቀን ለሚሰጥ ስልጠና ብር 4,000 (አራት ሺህ) እና ከሰባት ቀን በላይ ለሚሰጥ ስልጠና 7,000 (ሰባት ሺህ) ብር፤

4.2.3. በእቅድ በፕሮጀክቶች ለታያዙ አወደ ጥናት፣ ሴሚናር እና ስልጠና የማሰሉ ኩነቶችን እንዲያስተባብሩ በሚሾከተው የበላይ ኃላፊ ለሚመደቡና የተሰጣቸዉን ኃላፊነት በአጥጋቢ ሁኔታ ለተወጡ አስተባባሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) ይከፈላል፡፡ የአስተባባሪዎቹ ብዛት እንደ ፕሮጀክቱ ወስበስብነት የሚለያይ ሆኖ ከ 1 እስከ 5 ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

## 4.3. ለኘሮጀክት አስተባባሪዎች እና ተግባራዎች የማትጊያ ክፍያ

በወጭ ገንዘብ ድጋፍ የሚተገበሩ ኘሮጀክቶችን አፈፃፀም ለማሳለጥና ተጠባቂ ወጤቶች በጥራትና በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ እንዲቀርቡ ለማድረግ እንዲቻል በኘሮጀክት ለሚሰተፉ ኃላፊዎችና ባለሞያዎች የገቢ ግብር የሚከፈልበት ተመጣጣኝ ማትጊያ እንደሚከተለው ይከፈላል፡፡ የማትጊያ ክፍያው የሚፈፀመው ኘሮጀክቶቹ በቂ በጀት ካላቸውና በስምምነት ሰነዱ በግልፅ ማትጊያ (Staff time, Personnel or Honorarium) በሚል ሲሰፍር ይሆናል፡፡

4.3.1. በወጭ ገንዘብ ድጋፍ የሚተገበር ፕሮጀክትን ለሚመራ አስተባባሪ (Project Coordinator)፣ ግንባር ቀደም ተባባሪ ተመራማሪ (Principal Investigator)፣ ተባባሪ ተመራማሪ (Co-Principal Investigator)፣ እና የፕሮጀክት ተጠሪ (focal persons) **በፕሮጀክቱ የወል ስምምነት ሰነድ በተቀመጠው መሠረት** የማትጊየ ክፍያ ይከፈላል፡፡ አንድ ኘሮጀክት አንድ አስተባባሪ የሚኖረው ሲሆን፣ እንደ ኘሮጀክቱ ይዘት እና ተጠባቂ ወጤቶች ከአንድ በላይ ግንባር ቀደም ተመራማሪ፣ ተባባሪ ተመራማሪ እና የኘሮጀክት ተጠሪ ሊኖር ይችላል፡፡ ሆኖም ግን እንደ ኘሮጀክቱ ሁኔታ የኘሮጀክት አስተባባሪው የግንባር ቀደም ተመራማሪነትን የሥራ ድርሻ ደርቦ ሊይዝ ይችላል፡፡

4.3.2. ለኘሮጀክት ማስፈፀሚያ በቂ የማትጊያ በጀት (Staff time, Personnel or Honorarium) ተመድቦ ሆኖም አፈፃፀሙ በተመለከተ በኘሮጀክቱ የወል ስምምነት ሰነድ **በጥቅል የተቀመጠ** ከሆነ ወይንም ኘሮጀክቱን

በገንዘብ የሚደግፈው አጋር ድርጅት በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት **የውስጥ ደንብ እንዲከናወን ካማከተ** ወይንም ዝርዝሩ **በሚያሻማ ሁኔታ ያልተገለፀ** ከሆነ ወይንም **ሜጅመንቱ ተገቢ ሆኖ በሚገኘው ማንኛውም ምክንያት** የማትጊያ ክፍያው እንደሚከተለው ይፈፀማል፡፡

4.3.2.1 ለፕሮጀክት አስተባባሪ (Project Coordinator) እና ዋና (ግንባር ቀደም) ተመራማሪ (Principal Investigator) ለእያንዳዳቸው በወር 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) ብር ይከፈላል፤

4.3.2.2 ለተባባሪ ተመራማሪ (Co-principal Investigator) 10,000 (አስር ሺህ) ብር ይከፈላል፤

4.3.2.3 ለፕሮጀክት ተወካይ (Focal Person) በወር 5,000 (አምስት ሺህ) ብር ይከፈላል፤

4.3.2.4 ከላይ ከ4.3.3.1 – 4.3.2.3 መሠረት የተማከተወን ማጠን ለመክፈል ለማትጊያ የተመደው በጀት በቂ ሳይሆን ሲቀር የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ከበላይ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር የክፍያው ማጠን ይወሰናል፤

4.3.3. የውጭ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ከማሳለጥ አንፃር የተቋሙ የበላይ ሜጅመንት፣ የዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ (project planning & evaluation) እና የድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬቶች ከመደበኛው ስራቸው በተጨማሪ ለፕሮጀክቶች ትግበራ ወጤታማነት ጉልህ ሚና እንዳላቸው ይታመናል፡፡ እነዚህ የተቋሙ ባልደረቦች ከሥራቸው ፀባይ አኳያ ከአንድ ወይንም ከተወሰነ ፕሮጀክቶች ብቻ ጋር አስተዋፆአቸውን ማያያዝ ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም እነዚህ የተቋሙ ባልደረቦች ፕሮጀክቶች ለአጠቃላይ አስተዳደራዊ እና የጋራ ማልገያ ወጪዎች (Overhead Cost) ከሚሰባሰብ ቋት እንደሚከተለው ይከፈላል፡፡

4.3.3.1 የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር እና ምክትል ዋና ዳይሬክተር እያንዳንዳቸው በወር 15,000 (አስራ አምስት ሺህ) ብር፤

4.3.3.2 የዕቅድ፣ ክትትል እና ግምገማ ዳይሬክተርና ምክትል ዳይሬክተር በወር 7,000 (ሰባት ሺህ) ብር፤

4.3.3.3 የፋይናንስ ዳይሬክተር እና የውጭ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ክፍል ኃላፊ እያንዳንዳቸው ብር 5,000 (አምስት ሺህ) ብር፤

4.3.3.4 የምርምር ማዕከላት በውጭ የገንዘብ ድጋፍ የሚከናዎኑ ፕሮጀክቶች የሚተገበሩባቸው በመሆኑ የዕለት ተዕለት አስተዳደራዊ ድጋፍ ለሚያደርጉ የማዕከሉ ሜኔጅመንት ማትጊያ መከፈል ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ማዕከላት በውጭ ገንዘብ ድጋፍ ከሚከነዎኑ ፕሮጀክቶች ለአጠቃላይ አስተዳደራዊ እና የጋራ ማልገያ ወጪዎች (Overhead Cost) የሚያሰባስቡት አመታዊ ገንዘብ 200,000 (ሁለት መቶ ሽህ) ብር እና በላይ ሲሆን ለማዕከል ዳይሬክተር 3,500 (ሶስት ሽህ አምስት መቶ)፣ የፋይናንስ የስራ ሂደት ተጠሪ እና የፕሮጀክት አካውንታንት እያንዳዳቸው 1,000 (አንድ ሽህ) ብር የማትጊያ ክፍያ ይከፈላል፡፡

## 4.4 ለማትጊየ ክፍያ የሚያዝ በጀትን በተመለከተ

ለፕሮጀክት ማስተባበሪያ እና ትግበራ ማትጊያ (Staff time, Personnel or Honorarium) የሚያዘው በጀት ከጠቅላላው በጀት 35 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡ ሆኖም የፕሮጀክቱ ፀባይ አስገዳጅ ሆኖ ሲገኝ የበላይ ሜኔጅመንትን በማማከር በልዩ ሁኔታ ሊታይ ይችላል፡፡ የተቀመጠውን በጀት በደንቡ መሠረት መሆኑን የሚመለከታቸው የምርምር የሥራ ሂደት እና የዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች ይከታተላሉ፡፡

## 4.5 በፕሮጀክቶች የሚኖረን ተሳትፎ በተመለከተ

ተመራማሪዎች በውጭ የሚደገፍ ፕሮጀክቶችን ተፃፅፈው እንዲያመጡ፣ ፕሮጀክቶችም ሲገኙ በጥራት እና ስምምነት በተደረሰበት የጊዜ ገደብ መከናዎን ስለሚገባቸው ክህሎት፣ የበሰለ ልምድና በቂ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ተመራማሪዎች የሚኖራቸውን ተሳትፎ

ማኩላት የተቋሜን ወጪታማክት ከማሳደግ አንፃር ወሳኝ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ተመራማሪዎች በፕሮጀክቶች የማስተባበርና በግንባር ቀደምት ተመራማሪነት የሚኖራቸውን የተሳትፎ መጠን የትምህርት ዝግጅትን፣ የምርምር እና የሜጅመንት ልምድን በማገናዘብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

4.5.1 በረዳት ተመራማሪ II እና ተባባሪ ተመራማሪ የሥራ ደረጃ የሚገኙ በአንድ ወቅት (ተመሣሣይ ወቅት) በአንድ ፕሮጀክት የማስተባበር ወይም ግንባር ቀደም ተመራማሪነት ብቻ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ፈርጅ የሚገኙ ተመራማሪዎችን የሚፈጸምና የማስፈጸም አቅም በማገናዘብ የተቋሙ የበላይ ሜጅመንት ተጨማሪ አንድ ፕሮጀክት እንዲያስተባብሩ ሊወሰን ይችላል፡፡

4.5.2 በተመራማሪ I እና II የሥራ ደረጃ የሚገኙ በአንድ ጊዜ (ተመሣሣይ ወቅት) ፕሮጀክቶች የሚጠይቁት የሥራ ጊዜ እየታየ እስከ ሁለት በሚደርሱ ፕሮጀክቶች በአስተባባሪነት ወይንም በግንባር ቀደምት ተመራማሪነት ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

4.5.3 በከፍተኛ እና መሪ ተመራማሪ የሥራ ደረጃ የሚገኙ ተመራማሪዎች በአንድ ወቅት (ተመሣሣይ ጊዜ) እስከ ሦስት በሚደርሱ ፕሮጀክቶች በአስተባባሪነትና በግንባር ቀደምት ተመራማሪነት ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን ፕሮጀክቶቹ የሚፈልጉት የሥራ ጊዜና ተመራማሪው ያለበት የስራ ኃላፊነትና ጫና እየተመዘነ እና እየተገመገመ በተቋሙ የበላይ ሜጅመንት የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 4.6 መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ የተቋሙ የበላይ ሜጅመንት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 4.7 የመመሪያው ተፈፃሚነት

ይህ መመሪያ በኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ፊርማ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርናምርምር ኢንስትቲዩት ዋና ዳይሬክተር

ፊርማ፡

ቀን ፡